# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 137 ታህሳስ 21 ቀን 2003 ገጽ 1

**ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሰቆቃ ፈፃሚዎች ፍርዳቸውን ማግኘታቸው ፈጽሞ አይቀርም። ሰቆቃን ያስተናገዱ የወያኔ ካድሬ–ዳኞች፣ አቃብያነ ህግ፣ ፓሊሶችና ሌሎችም ሹማምንት ተገቢውን ቅጣት ማግኘታችው በጭራሽ አይቀርም። ያኔ "ታዝዤ ነው የፈጸምኩት" ማለት እንደማያዋጣ ዛሬውኑ እንነግራቸዋለን። ይህ ቀን መምጣቱ በጭራሽ አይቀርም።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔው ውጪ ጉዳይ ሚንስቴር መሬት ለባዕዳን እንደሚሸጥ አስታወቀ

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ሎሌ የሆነው ሃይለማርያም ደሳለኝ በቅርቡ በህንድ አገር ባደረገው ጉብኝት ለአንድ የቴሌቪዥን ድርጅት በሰጠው ቃለ መጠይቅ አገዛዙ መሬትን ለውጪ አገር ባለሃብቶች ለመሸጥ ዝግጅት ላይ እንዳለ አስታወቀ።

ሃይለ ማሪያም ደሳለኝ አይ ቲ ኤም ከተባለው የህንድ ቴሌቪዥን ጋር ባደረገው ቃለመጠያ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የመሬት ችብቸባ በአለማቀፍ መገናኛ ብዙሃን እና የሙብት ተሟጋች ድርጅቶች እየተገለጸ እንዳለው የመሬት ቅሚያ አይደለም ሲል መናገሩ ለሹመት ካበቁት ጌቶቹ በረከት ስምዖንና መለስ ዜናዊ የቀሰመው ቅጥፈት እንደሆነ ቃለመጠይቁን የተከታተሉ አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው። ለውጪ ጉዳይ ሚንስቴርነት ከተሾመ የመጀመሪያው በሆነው በዚህ ጉብኘት ወቅት በሰጠው እርስ በርሱ የተምታታ መግለጫ ፤ በአንድ ጎን ኢትዮጵያ ትልቅ መሬት ስላላት የመሬት ችብቸባው ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን ከይዞታቸው የሚያፈናቅል አይደለም ካለ ቦኋላ መልሶ ደግሞ ትላልቅ እርሻዎች እየተስፋፉ ሲሄዱ፣ የትናንሽ ገበሬዎች ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል ሲል መደመጡ ብዙዎችን አስገርሞአል።

በዚህ ቃለ መጠይቅ ከተገለጹት ጉዳዮች ውስጥ እጅጉን አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው ወያኔ አርሶ አደሩን እያፈናቀለና ብርቂዬ የተፈጥሮ ደን እያስመነጠረ የአገሪቱን ለም መሬት በርካሽ ዋጋ ለዘመናት በኪራይ እየቸበቸበ መሆኑ አንሶት እስከነጭራሹ በሽያጭ ለባዕዳን አሳልፎ ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆኑ ነው። አያት ቅድሜ አያቶቻችን ባዕዳን አገራችንን በወረራ እንዳይይዙና ህዝቡን ለባርነት እንዳይዳርጉት ውድ ህይወታቸውን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው የሚፈጸመውን ሰቆቃ እያወገዙ ነው

በአለም ዙሪያ የሚገኙ የኢትዮጵያውን ማህበራት እና ግለሰቦች የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በእናት አገራቸው በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ እያወገዙ ነው።

የኢትዮጵያውያን ሴቶች የሰብአዊ መብት ጥምረት የተባለው ድርጅት ባለፈው ሳምንት ባወጣው መግለጫ የሶስት ልጆች እናት የሆኑ ሴት ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ስለመሆኑ ማስረጃ እንደደረሰው ገልጿል። ድርጅቱ በመግለጫው፥ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ የተባሉት እና በ2001 መንግስት በመገልበጥ ሙከራ ተከሰው ከታሰሩት ውስጥ ብቸኛዋ ሴት የሆኑት እናት ስለደረሰው ሰቆቃ ዘርዝሯል።

ወ/ሮ እማዋይሽ እይናቸው በጨርቅ ተሸፍኖ እና እጃቸው በሰንሰለት ታስሮ ወደ ስቃይ መነዳታቸውን፤ እጃቸው ታስሮ መሰቀላቸውን፤ እግራቸው መገረፉን፤ እንዲሁም የውስጥ ታፋቸው፣ መቀመጫቸው እና እጆቻቸው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ዜጎችን በማስገደድ ቦንድ ሊያስገዛ እየተሰናዳ ነው ተባለ

የኢትዮጵያን መንግስት በጉልበት ተቆጣጥሮ የሚገኘው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ፥ የገጠመውን የገንዘብ እጥረት ለመወጣት ዜጎችን እያስገደደ ቦንድ ሊያስገዛ እየተሰናዳ መሆኑን የሚጠቁም ዘገባ ለዝግጅት ክፍላችን ደርሷል።

ዘረኛው አገዛዝ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እና ለባለስልጣናቱ የዘረፋ እድል ለመፍጠር ሲል ብቻ አቅሙን ሳያገናዝብ ያወጣው የአምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተብዬ ከፍተኛ የገንዘብ ጫና እንደፈጠረበት የተለያዩ ዘገባዎች ሲያሳዩ ቆይተዋል።

ከዚህ ቀደም የአገዛዙ ዋና አበዳሪ ከሆኑት ተቋማት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀማጭ ገንዘብ ቀውስ ላይ በመሆኑ፣ ማህበራት እና ዜጎች የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ጫና ሲደረግባቸው (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ ህዝብ በዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች ላይ የበቀል እርምጃን መውሰድ ጀመረ

ለፍትህ ጩኸቱ መልስ ያልተገኘለት የኢትዮጵያ ህዝብ፥ በዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች ላይ የበቀል እርምጃዎችን መውሰድ እንደጀመረ የሚያሳዩ ዘገባዎች መሰማት ከጀመሩ ሰነባብተዋል።

ከአንድ ወር በፊት መሬቶቻቸውን የተቀሙ የሰሉልታ ከተማ ነዋሪዎች በአገዛዙ ሹመኞች እና በአባሪዎቻቸው ላይ ጥቃት መፈጸማቸው በኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና በግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ ተዘግቦ እንደነበር ይታወቃል።

ከሁለት ወራት በፊትም እንዲሁ በአላማጣ ከተማ ከንቲባ ላይ በቁጣ የተነሳሳ ጥቃት ተፈጽሞአል። ባለፈው ማክሰኞ ደግሞ በጋምቤላ ክልል ከዘረኛው አገዛዝ ጋር ትስስር አለው ተብሎ የሚገመት ነጋዴ በአሰቃቂ ሁኔታ ስለመገደሉ ከስፍራው ለግንቦት 7 ድምጽ መረጃ ተልኮለታል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ከሰሞኑ በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ሳሪስ በመባል በሚታወቀው አካባቢ አንድ የትግራዩ ገዢ ቡድን ካድሬ መጠጥ ቤት ውስጥ በወጣቶች ተደብድቧል። የደረሰን መረጃ እንደሚገልጸው፥ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በርካታ ነጋዴዎች አገር ጥለው በሽሽት ላይ እንደሚገኙ ተዘገበ

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ግብር ባለመክፈል እና በመሳሰሉት ክሶች ሽፋን ከትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በሚደርስባቸው ጥቃት ምክንያት ከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንደሚገኙ ተደጋጋሚ ዘገባዎች ሲያሳዩ ቆይተዋል።

ፎርቹን የተባለው እና ለአገዛዙ ቅርበት ያለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ፥ በርካታ ነጋዴዎች ከዚህ ስጋት የተነሳ አገር ጥለው መውጣታቸውን ገልጿል። እንደ ጋዜጣው ዘገባ፥ በተለይ ከመሬት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ተፈጽሟል በሚባል ሙስና የከተማዋ ሹመኞች ብዙ ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ እንዳሉ መታወቁ የስጋቱን ደረጃ ከፍ አድርጎታል።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የአገሪቱን የንግድ ዘርፍ በሙሉ ከአንድ ዘር በተውጣጡ ምርጦች ቁጥጥር ስር ለማዋል ሩጫ ከጀመረ መቆየቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ፥ ብዙ የዋህ ነጋዴዎች ለህዝቡ ሰቆቃ ጆሮባቸውን በመስጠት ለገዢው ቡድን ገንዘብ በገፍ ቢለግሱ ንብረቶቻቸውን ማትረፍ የሚችሉ መስሏቸው ሲለፉ ቆይተዋል። በርግጥም አንዳንዶቹ ነጋዴዎች ለጊዜውም ቢሆን ከዚህ ጥቅም ማግኘታቸው ይታወቃል። ቢሆንም ግን፥ ባለፈው የምርጫ ተውኔት ግርግር ዘረኛውን አገዛዝ በመርዳት የኢትዮጵያን ህዝብ የካዱት ነጋዴዎች ሳይቀሩ ከዚህ ጥቃት እንደማይተርፉ የፎርቹን ዘገባ አመልክቷል።

ነጋዴዎቹ በመተባበር ለዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ የላኩት ተማጽኖም ምንም ውጤት እንዳላስገኘ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህም የተነሳ በርካታ ታዋቂ ነጋዴዎች ባለፉት ሳምንታት አገር ጥለው መውጣታቸው የአጋጣሚ ጉዳይ እንዳልሆነ ጋዜጣው ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል።

## የውሃና የመብራት እጥረት የከተማ ነዋሪዎችን አማሯል

የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከስልሳ ስምንት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ተፈናቃይ ገበሬዎች ስራ የሚፈጥር ኢንዱስትሪ እገነባለሁ ብሎ በሚፎክርበት ዘመን፣ በአገሪቱ ውስጥ ያከናወነው የመሰረተ ልማት ግንባታ እንኳን በሺዎች የሚቆጠሩ ፋብሪካዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችንም መደገፍ አቅቶታል።

አገዛዙ እንደ አዲስ አበባ ላሉ አለማቀፍ ከተማዎች እንኳ ሳይቀር መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ ተስኖታል።

ግልገል ጊቤ ሁለት እንደገና ተጠግኖ ስራውን ጀምሯል በተባለበት ሳምንት በአገሪቷ ዙሪያ ያሉ ከተሞች መብራት በፈረቃ ማግኘታቸውን ቀጥለዋል። የውሃ ችግርም የተስፋፋ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ በተለይ አንዳንድ የመዲናይቱ ነዋሪዎች በሁለት ሳምንት አንዴ ብቅ እንደሚልላቸው ይናገራሉ። የደብረ ዘይት ከተማ ህዝብ የውሃ አገልግሎት ሳያገኝ አራት ወር ሊሞላው እንደሆነ ባለፈው ሳምንት መዘገባችን ይታወሳል።

ዘጋቢያችንን ያናገሩት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፥ የመብራት እና የውሃ እጥረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚሉት ልማት የፈጠረው ችግር እንጂ ተራ ችግር አይደለም ሲሉ ተሳልቀዋል።

# ርእሰ አንቀጽ

## ለወያኔ ሰቆቃ ምላሻችን ምንድነው?

በወያኔ የወንጀል ምርመራና የእስር ቤቶች አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ አገር ወዳድ የፖሊስ፣ የፌደራልና የደህንነት ባልደረቦች በኢትዮጵያ እስር ቤቶች እየተፈፀመ ስላለው ሰቆቃ የላኩት ሪፓርት ይፋ ከሆነ ወዲህ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እንቅልፍ አጥተዋል። “ምን እናድርግ?” የሚሉ ጥያቄዎችም ተበራክተዋል።

ሪፓርት አቅራቢዎቹ ራሳቸው ከእኛ ምን እንደሚጠብቁ ግልጽ በሆነ አቀራረብ አብራርተውልናል። እነሱ ያሉንን እንደገና እናጢነው።

*እኛም ይህን ሪፓርት ለእናንተ ለወገኖቻችን ስንልክላችሁ አንድ ሰሞን ጉድ ብላችሁ እንድትረሱት አይደለም። እኛ በራችንን ዘግተን፤ ጨለማን ተገን አድርገን አልቅሰናል። እናንተም እንደ እኛ አልቅሱ ... አልቅሳችሁ ግን ዝም እንድትሉ አይደለም። በተለይ በውጭ ሃገር የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ሃገር እስር ቤቶች ውስጥ የሚፈፀመውን በዘር የተደራጀና በዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት፤ በግለሰቦች ላይ የሚዘንበው ሰቆቃ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የዓለም የቀይ መስቀል ድርጅት፣ የህይውማን ራይትስ ወች፣ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የጀኖሳይድ ወች ድርጅት፣ በሄግ የሚገኘው የዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት፣ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት፣ የአውሮፓ ፓርላማ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሌሎችም በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ግፎችን የሚዘግቡ፣ ወንጀለኞችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚታገሉ ሁሉ እንዲያውቁት እንድታደርጉ ነው። “ምን ዋጋ አለው?” ትሉን ይሆናል። አዎን ዛሬ ምንም ዋጋ ላይኖረው ይችላል። ብዙዎቹ መንግስታትና ድርጅቶች የወያኔን ግፈኝነትና ጨካኝነት ያውቃሉ። ... ይህንን እያወቁ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ወያኔ ለሚፈጽመው ወንጀል ተባባሪ መሆንን መርጠዋል። ወያኔን በከፍተኛ ደረጃ በገንዘብ የሚደጉሙት በዲፕሎማሲ መድረክ እክል እንዳይገጥመው ድጋፍ የሚያደርጉለት ሆነው አርፈውታል። ...*

*ይህንን መረጃ ስንልክ ዛሬውኑ አንድ ነገር ይሆናል ከሚል ቅዠት አይደለም። ነገ የሚባል ነገር መኖሩን መርሳት የለብንም። የዛሬ የሃገራችን እብሪተኛ ገዢዎች ነገ ቀን ሲጎድልባቸው እነዚህን መረጃዎች አሰባስበው ከሳሽ ለመሆን የሚሽቀዳደሙት እነዚህ እንደ ወያኔ ይሉኝታ የማያውቁ የምዕራብ ሃገሮች ስለሆኑም መረጃው በእጃቸው ቢገባ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ለማለት ነው። አቅም ያላችሁ ይህንን ዘገባ ተርጉማችሁ ለምዕራብ የሚዲያ ሰዎች፣ የሰው ልጅ መብት ሲጣስ ለሚያሳስባቸው የፓርላማ ተመራጮች፣ የሲቪል መሪዎች አድርሱልን።*

*በእናንተ በወገኖቻችን በኩል የሚደረገው ይህ ብቻ አይደለም። ይህ ብቻም በቂ አይሆንም። ... ከወያኔ ዘረኝነት የሚመጣ ጭካኔ ያላረፈበት ዘር በሃገሪቱ ውስጥ አይገኝም። የኦሮሞው፣ የጋምቤላው፣ የኡጋዴኑ፣ የሲዳማው፣ የጉጂው እና የሌላውም ዘር ስቃይና መከራ ምድሪቱ ከምትሸከመው በላይ ሆኗል። ይህንን ተረድታችሁ ይህንን በሁሉም የሃገሪቱ ህዝብ ላይ የሰለጠነ የዘረኞች ጭካኔ እንዲያከትም ተባብራችሁ እንድትነሱ ነው።*

*ሌላው ፍላጎታችን ዜጎች ይህንን መንግስት እንደ ጤነኛ መንግስት በመውሰድ ከዚህ መንግስት ጋር እስካሁን የገቡበትን ማናቸውንም ግኑኝነት በቅጡ እንዲፈትሹ ነው። በእኛ እምነት ከዚህ መንግስት ባለስልጣናት ጋር የሚወዳጁ፤ ከዚህ መንግስት ጋር ተሻርከው የሚነግዱ፤ በዚህ መንግስት ግብዣዎች ላይ የሚገኙ፤ ይህ መንግስት የሚጠይቃቸውን የሚፈጽሙ የሃገሪቱ ዜጎች ከምን ዓይነት ጨካኝ አረመኔ ሰዎችና መንግስት ጋር እየሰሩ እንደሆነ እንዲያውቁት ነው። ... ከዚህ ወንጀለኛ መንግስትና ባለሥልጣናት ጋር ስራችንና ኑሯችን ከሚያስገድደን በላይ መወዳጀት እራሱ ወንጀለኛ ሊያደርገን እንደሚችል ማወቅ ይኖርብናል።*

በእውነቱ ከዚህ በላይ ምን ማለት ይቻላል? እነዚህ አገርወዳድ ዜጎች በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ እየተፈጸሙ ያሉ ሰቆቃዎችን፤ የሰቆቃ ፈጻሚዎችን ስም፤ በወያኔ ዳኝነትና በሰቆቃ መካከል ስላለው ትስስር ሁሉንም በዝርዝር ገልፀውልናል። እነሱ እንዳሉት ለአንድ ሰሞን “ጉድ” ብለን፤ ከንፈሮቻችንን መጥጠን፤ በየግላችን አልቅሰን ዝም እንዳንል ማድረግ ያለብንን ጭምር ዘርዝረው ጽፈዋል።

እኚህ አገር ወዳዶች የጣሉብንን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁዎችና ብቁዎች ነንን? መልሳችን “አዎን!” ከሆነ ለጥሪዓቸው ተግባራዊ ምላሽ እንስጥ፤ በፀረ ሰቆቃ ትግል እንሳተፍ። በየደረስንበት በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን ግፍ እናጋልጥ። በቦሌ፣ በካሣንቺስ፣ በአራት ኪሎ፣ በፒያሳና በጉለሌ “የጨዋ” መኖሪያዎች የሚመስሉ ቪላዎች ወገኖቻችን ፍዳቸውን የሚያዩባቸው ድብቅ እስር ቤቶች መሆናቸው አንዘንጋ። ቡና ቤቶችና የባህል ሙዚቃ ቤቶች ጨኸት አገር ሰላም የሆነ ቢያስመስሉም እዚያው እጎናቸው ያለው ቤት ውስጥ ግን የሰዎችን አፍ ከካልሲ ወትፈው በኤሌክትሪክ ሽቦ በመጥበስ የሚዝናኑ አውሬዎች እንዳሉ አንዘንጋ።የወያኔ ድብቅ እስር ቤቶች ያሉት በየሰፈሩ እንጂ ሩቅ ቦታ አይደለም። አንዳንድ ወገኖቻችን በገዛ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በቤተሰቦቻቸው ፊት ተሰድበዋል፣ ተረግጠዋል፣ ታስረዋል፣ ተደብደበዋል።

ደጋግመን እንደገለጽነው በማናቸውም ምክንያት ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሰቆቃ ፈፃሚዎች ፍርዳቸውን ማግኘታቸው ፈጽሞ አይቀርም። ሰቆቃን ያስተናገዱ የወያኔ ካድሬ—ዳኞች፣ አቃብያነ ህግ፣ ፖሊሶችና ሌሎችም ሹማምንት ተገቢውን ቅጣት ማግኘታችው በጭራሽ አይቀርም። ያኔ “ታዝዤ ነው የፈጸምኩት” ማለት እንደማያዋጣ ዛሬውኑ እንነግራቸዋለን። ይህ ቀን መምጣቱ በጭራሽ አይቀርም። ያኔ ተጠያቂዎቹ ከላይ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም። “ምን ማድረግ እችላለሁ?” እያሉ ከንፈሮቻቸው መጠው የቀሩትም ቢሆን ከተጠያቂነት፤ እጅግ ቢያንስ ከህሊና ፀፀት አያመልጡም።

ያ ቀን መች ነው? ያ ቀን በቶሎ እንዲመጣ ምን እናድርግ? መረጃውን ያደረሱን ወገኖቻችን “ስቃይና መከራ ምድሪቱ ከምትሸከመው በላይ ሆኗል!!! .... የዘረኞች ጭካኔ እንዲያከትም ተባብራችሁ ተነሱ” ብለውናል። የኛ ምላሽ ምንድነው?

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የወያኔው ውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ... (ከገጽ 1 የዞረ)

እንዳልገበሩ፤ አገር በቀል የሆነው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በያዘው መሳሪያ ህዝባችንን በማፈን አገራችንን ለውጪ ባለሃብቶአች በመሸጥ ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ ባርነት ቀንበር ሊያሸክምን በዝግጅት ላይ መሆኑ ወያኔ እስከ ዛሬ እየፈጸመ ካለው ወንጀል ሁሉ የከፋ እንደሆነ ለግንቦት 7 ድምጽ አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ አገር ወዳድ ተናግረዋል። ሃይለማርያምን ቃለ መጠይቅ ያደረገው ህንዳዊ ጋዜጠኛ፥ የኢትዮጵያው አገዛዝ ለባዕድ አገራት ነጋዴዎች የመሬት ሽያጭ ሊጀምር እያቀደ መሆኑንና በአገር ውስጥ ከፍተኛ ውዝግብ እያስነሳ ላለው ለዚህ የመሬት ጉዳይ ወደፊት ሊተካ የሚችለው መንግሥት ድርጊቱን ሊቀለብስ ቢችል ባለሃብቶች ምን ዋስትና ይኖራቸዋል ብሎ ለሰነዘረው ጥያቄ ፤ መሬትን አስመልክቶ በአገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ምንም ተቃውሞ እንደሌለውና ተቃውሞ ያለ የሚያስመስሉት በአገሪቱ ውስጥ እየተፈጸመ ስላለው ምንም የማያውቁ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶች ናቸው ሲል ተደምጦአል።

ሃይለማርያም ደሳለኝ በቃለ መጠይቁ ወቅት፥ እንደ ጋምቤላ ባሉ ጠረፋማ ክልሎች አብዛኛው መሬት በጥቅም ላይ አይውልም ሲል ሲቀጥፍ ተስተውሎአል። በቅርቡ ለእንግሊዙ የመረጃ ኩባንያ ቢቢሲ ቃላቸውን የሰጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ግን በከብት እርባታ የሚተዳደሩትን ጨምሮ ህዝቡ በየወቅቱ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ፍራፍሬዎችን በመልቀም የሚኖር እንደሆነና፤ በባህላቸው መሬት የህዝቡ እንጂ የማንም እንዳልሆነ አስረድተዋል። እንደ ሶማሌ እና አፋር ባሉ እና በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች መሬታቸውን እየተቀሙ ባሉባቸው ክልሎችም አብዛኛው ህዝብ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር የከብት አርቢ እንደሆነ ይታወቃል።

ከሰማንያ አምስት በመቶ በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን በግብርና ስራ የሚተዳደሩ መሆናቸውን እና አማራጭ የስራ እድል ሊፈጥር የሚችል የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በአገሪቱ እንደሌለ ለሚረዱ ዜጎች፣ የሃይለማርያም አባባል “ውሻ በበላበት ይጮሃል” ከምል የአበው አባባል የተለየ ሃቅ እንደሌለው ግልጽ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከብጣሽ መሬታቸው በሚያገኙት ገቢ ቤተሰባቸውን ማስተዳደር የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች በከፍተኛ ቁጥር ወደ ትላልቅ ከተሞች እየተሰደዱ በልመና መሰማራት መጀመራቸው እና በቅርቡም በጠረፋማ ክልሎች የሚኖሩ ገበሬዎች ከየቀዬያቸው ተፈናቅለው ለባዳ አገር ነጋዴዎች ቦታ እንዲለቁ እየተደረጉ መሆኑን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ሲገለጽ እንደነበረ አይዘነጋም። በጋምቤላ ቀዬያቸውን እንዲለቁ ሲታዘዙ የተቃወሙ ግለሰቦች እስከ ግድያ የሚደርስ ቅጣት እየተካሄደባቸው መሆኑ ባለፈው ሳምንት ለአሜሪካ ድምጽ የአማሪኛው ዝግጅት ቃላቸውን የሰጡ የአካባቢው ነዋሪ መናገራቸው ይታውቋል። በአሁኑ ሰዓት በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአገሪቱ ከተሞች በልመና እንደሚተዳደሩ የሚታወቅ ሲሆን፤ በቅርቡ እየተፋፋመ የሄደው የመሬት ቅሚያ ሰለባዎች የሆኑት ወደየከተሞች መፍለስ ሲጀምሩ የሚከሰተው ችግር ለበርካቶች መገመት ከሚችሉት በላይ ሆኗል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## የወያኔ የመሬት ፖሊሲና የገበሬው ሰቆቃ

መሬት ለኢትዮጵያውን ገበሬወች የህልውናቸው እስትንፋስ ነው:: ለኢትዮጵያውን መሬት ከምጣኔ ሀብታዊ መተዳደሪያነቱ ባሻገር የአርነታቸው ነጸብራቅም ነው:: በተለያዩ ስርዓቶች ገበሬው ላይ ሲደርሱ የነበሩና እየደረሱ ያሉት ግፍና ሰቆቃ የገበሬውን እና የመሬቱን ጥብቅ ቁርኝት መነሻ በማድረግ ነው:: ቀደም ባሉት ጊዜያት ገበሬው ጭሰኛ : ገባር ነበር አሁንም በወያኔ ጭፍን የመሬት ፖሊሲ ምክንያት ገበሬው የባለቤትነት መብቱ ተነጥቆ ተከራይ ሆነል:: ለዘመናት ጥሪቱንና ላቡን ያፈሰሰበትን መሬት በአንድ ጀምበር ተንጥቆ በእኛ እናውቅልሀለን የአምባገነኖች የመሬት ፖሊሲ ወደ ባሰ ድህነት ተሸጋግሩአል:: የወያኔው አገዛዝ በአንድ ወገን ነጻ ገበያ አራምዳለው እያለ በሌላ በኩል የመሬት የግል ባለቤትነት መብት መንፈጉ- መሬት እንድ አንድ ካፒታል ገበያው ውስጥ በመግባት የራሱን አስተዋጽኦ እንዳያበረክት እንቅፋት ሆኖበታል::

ከእጅ ወደ አፍ በሆነው ኑሮ ምክንያት ገበሬው ሌላ ቋሚ ንብረት ማፍራት ባለመቻሉ መሬቱ ላይ የሚመነጩትን ድርብ መብቶች (bundle of rights ) እንዲጠቀምበት የሚያበረታቱና የሚያስቹሉ የመሬት ፖሊሲወችን መንደፍ የአንድ ሀላፊነት የሚሰማው መንግስት የቤት ስራ ነው:: የዜጎች የሀገሪቱን ሀብት በእኩል የመጠቀም መብት ቅድሚያ ሊሰጠውና ትኩረትም ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው:: መንግስት እንደ አንድ ባለድርሻ አካል የሀገሪቱን ሀብት እኩል ከዜጎች ጋር ሊጠቀምና ሊያስተዳድር መብትና ስልጣን ከህዝብ ተሰጠው እንጅ ከዚያ አልፎ አሁን እንደምንመለከተው የወያኔው አገዛዝ የዜጎችን መብት መገደቡ የዚህ ስርኣት አምባገነንነት አይነተኛ መገለጫ ነው::

በተጨማሪም የወያኔው አገዛዝ እየተከተለ ያለው አሰራር የመሬት ፖሊሲውን ኢ-ፍትሀዊነት ይገልጽ እንድሆን እንጂ ለገበሬው ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ ለውጥ ሲያመጣ አልተስተዋለም:: የከተማው ነዋሪ በገበሬው ላይ ጥገኛ ከመሆኑም በላይ በአንጻሩ በከተሞች ለገበሬው የሚሆን ምቹ የስራ እድል ባለመኖሩ የገበሬው የዛሬውም የወደፊቱም ተስፋ በመሬቱ ላይ እንዲወሰን አስገድዶታል:: በየአምልኮ ቤቱ ደጃፍ ላይ ተቀምጦ ምጽዋት የሚለምነውና : መሬቱን በወያኔው አምባገነን አገዛዝ ጫና (ደላላነት) ለውጭ ኢንቨስተር አሳልፎ ሰጥቶ ወደውጭ ሀገር የሚሰደደው ገበሬ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የመሬት ፖሊሲ ውጤት ነው::

በመስኩ የተሰራ ጥናትን ዋቢ በማድረግ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ልሳን የሆነው "አዲስ ምእራፍ" መጽሔት እንዳሰፈረው በሀገሪቱ ከ200,000 የማያንሱ ወገኖች በልመና ላይ ተሰማርተው በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ:: ከእነዚህም መካከል አብዛኛወቹ ከተለያዩ ክልሎች የመጡ በግብርና ስራ ይተዳደሩ የነበሩ መሆናቸው በግልጽ ይታያል:: ገበሬው አቅራቢ እንጂ ተጠቃሚ ሊሆን ባለመቻሉ ኑሮው ከእለት እለት እያሽቆለቆለ ሄዱአል:; ይሁን እንጂ ባንጻሩ የወያኔው አገዛዝ የሚዲያ ጀግኖች "ሞዴል አርሶ-አደሮች" የስርኣቱ አሸርጋጆች ምልምል የገበሬ ካድሬወች እንጅ ምስኪኑን የኢትዮጵያ ገበሬ እንደማይወክሉ የኢትዮጵያ ህዝብ አሳምሮ ያውቀዋል:: የሚዲያ ጀግኖቹ ማስታወቂያ ወያኔ በህዝብ ዘንድ ያለውን መጥፎ ስም ለመቀየር የሚጠቀምበት ስትራቴጂ እንጅ ከሌላው ገበሬ የበለጠ ተጨባጭ ለውጥ እንዳላመጡ ይታወቃል::

ወደዋናው ነገር ስንመጣ የወያኔን የመሬት ፖሊሲ በተመለከተ ትልቁ ተግዳሮት ከዚህ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል:በመጀመሪያ የይዞታ ዋስትና አለመኖር (Tenure insecurity) ትልቁ ችግር ነው:: የመሬት ባለቤትነት በኦፊሲል ከወያኔው አምባገነን አገዛዝ እጅ ስር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ገበሬው በይዞታው ላይ የእነነት ስሜት እንዲያጣ:: የይዞታ ዋስትና አለመኖር የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ አለው : ገበሬው መሬቱን እንደራሱ ሀብት አድርጎ ይዞ ዘላቂ ልማት እንዳያከናውን እንቅፋት ሆኖበታል:: የመሬቱን ለምነትና ስነ-ምህዳራዊ ደህንነት ጠብቆ ከማምረት ይልቅ ጊዜያዊና ገበያ ላይ ብቻ አትራፊ ይሆናሉ ያላቸውን ምርቶች ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ተግዶአል:: በዚህም ምክንያት ሸማቹ የሚፈልገውና ገበሬው የሚያመርተው ባይነትም ሆነ በመጠን ሊጣጣም አልቻለም:: ከዚሁ ቁልፍ ችግር በተጨማሪም የይዞታ ዋስትና አለመኖር ዘለቄታዊ ኢንቨስትመንትን በእጅጉ ያዳክማል :: ከሁሉም በላይ ገበሬው በማሳው ላይ ዛፍን እንዳይተክል ትልቅ እንቅፋት በመፍጠሩ ገበሬው የማሳውን አፈር መከላት መቆጣጠር ካለመቻሉም በላይ የማሳውን ለምነት መራቆትና ምርት አልባ መሆን መከላከል አለመቻሉን መጥቀስ ይቻላል:: የመሬት መራቆት ችግር ድምር ውጤት ደግሞ ከገበሬው ክልል አልፎ በዓለማችን እየታየ ላለው የአየር ንብረት መዛባት የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ማለት ነው::

በኢንቨስትመንት ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገም የማሳውን ባለቤት ራሱ ገበሬውን በኢኮኖሚና በተክኖሎጂ አቅሙን በማሳደግ (በማጠናከር) የለውጥ ሀይል ማድረግ ሲቻል-ገበሬው በአምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ መሬቱን ተነጥቆና በገዛ ሀገሩ አይኑ እያየ መሬቱ ለባእዳን ተሰጥቶበት የፍትህ ያለህ እያለ ይገኛል::

በሁለተኛ ደረጃ የአምባገነኑን ወያኔ የመሬት ፖሊሲ በተመለከተ የገበሬው ተግዳሮት መሬት የማግኘት መብት (access to land )ችግር ነው:: ምንም እንኳ ህገ-መንግስቱ ማንኛውም እድሜው ከ18 አመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በግብርና ስራ ለመተዳደር ፍላጎት ያለው ያለምንም ክፍያ መሬት ማግኘት ይችላል ቢልም በተግባር ሲታይ ግን እየሆነ ያለው ተቃራኒ ነው:: ለምሳሌ ብዙ ወጣቶች መሬት ይሰጠን ብለው ሲጠይቁ በማህበር ካልተደራጃችው አንሰጥም እንደሚባሉና በማህበር ሲደራጁ ደግሞ ለእናንተ የሚሆን ከሌሎች ባለይዞታወች ላይ ተቆርሶ ስለሚሰጣችው የመሬት ክፍፍል እስኪደረግ ጠብቁ እንደሚባሉ በምሬት ይገልጻሉ:: እነዲህ አይነቶቹ ወጣቶች ሌላ ምንም አይነት አማራጭ ሰለሌላቸው ወይ ለልመና ይዳረጋሉ አለያም ሀገር ጥለው ይሰደዳሉ::

እንደ አብነት ለመጥቀስ የዚህ ጽሁፍ ጸሀፊ በስራ አጋጣሚ ያነጋገራቸው የምእራብ ጎጃም ዞን የጎንባት ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ ገበሬወች እንደገለጹት "ምንም እንኳ ሰፋፊ መሬት ባካባቢያችን ቢገኝም በአጥር ተከልሎ ለውጭ ባለሀብቶች ለአበባ እርሻ ተቀምጡአል " በማለት ተናግረዋል:: እነኝሁ ገበሬዎች ከመሬት እጦት የተነሳ በአካባቢው ወጣት ጥፋተኞች እንደተበራከቱ አክለው ገልጸዋል::

ባጠቃላይ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ገና በጠዋቱ በስልጣን ወምበር ላይ ሲኮፈስ ለመሬት ፖሊሲው ልዩ ትኩረት በመስጠት አሁን እየተከተለ ያለውን አሰራር እንዲተገብር የወሰነበት ቁልፍ ምክንያት መሬትን ለፖለቲካ ጥቅም በማዋል የሃገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ 80 በመቶ የሚሸፍውን ገበሬ በቁጥጥሩ ስር በማዋል እንደፈለገው ለመድረግ የወጠነው ረቂቅ ሴራ እንደሆነ በርካታ ምሁራን ሲገልጹ መቆየታቸው ይታወቃል ::

## የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ዜጎችን በማስገደድ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መቆየቱን መዘገባችን ይታወሳል። በተጨማሪም፥ ለምሳሌ የአዲስ አበባ መስተዳደር የከተማይቱ ህዝብ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር እንዲያዋጣለት በመጠየቅ የጠራራ ጸሃይ ዘረፋ ማካሄድ መጀመሩ በሰፊው ተዘግቦ ነበር።

አገዛዙ በህዳር ወር ለአለማቀፉ የገንዘብ ተቋም አይ.ኤም.ኤፍ በላከው ደብዳቤ የአንድ አመት እድሜ ያላቸውን የቴረዠሪ ቦንዶች በየሳምንቱ መሸጥ ሊጀምር መሆኑን ገልጾ ነበር። የትሬዠሪ ቦንድ ሽያጭ መንግስታት ወይም ተቋማት የገንዘብ እጥረት ለመወጣት የሚወስዱት እርምጃ ነው። ነገር ግን ይህ እንደማንኛውም ግዢና ሽያጭ፥ በገዢው ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው። ለአይ.ኤም.ኤፍ. በተላከው ደብዳቤ ያልተጠቀሰው ግን ሽያጩ የሚካሄደው በግዳጅ መሆኑ ነው።

ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፥ አገዛዙ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሚከፍታቸው ባንኮች አማካይነት የትሬዠሪ ቦንዶችን በግዳጅ ለመሸጥ የሚስጥር እቅድ እያሰናዳ ነው። ዘጋቢያችን ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው፥ ይህ እቅድ እያንዳንዱ አባወራ እና ስራ ያለው የቤተሰብ አባል አምስት መቶ ብር የሚያወጣ ቦንድ እንዲገዛ ግዳጅ ይጥላል። አገዛዙ በዚህ አኳኋን በአስርት ቢሊዮን ብር የሚቆጠር ገንዘብ የማሰባሰብ ተስፋ እንዳለውም ለማወቅ ተችሏል።

## የኢትዮጵያ ህዝብ በዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በካድሬው ላይ ለደረሰው ጥቃት መነሻ የሆነው ሙዚቃ እንዲለወጥ የመጠጥ ቤቱን ሰራተኞች በቁጣ ማዘዙ ነበር።

ከጥቂት አመታት ወዲህ በከፍተኛ ማናለብኝነት የሚንቀሳቀሱት የአገዛዙ ካድሬዎች በየመሸታ ቤቱ እየገቡ አገዛዙ የማይወደው የቴሌቪዥን ጣቢያ እንዲለወጥ ወይም ሙዚቃ እንዲቀየር እንደሚያዙ እና ይህንን በሚቃወሙ ታዳሚዎች ላይ ሽጉጥ እየመዘዙ ህዝብ እንደሚያሸብሩ ይታወቃል። ይህ አይነት ሁኔታ በተደጋጋሚ የገጠማቸው ሶስት ወጣቶችም እራሳቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው ግለሰቡን ክፉኛ እንደደበደቡት እና በአሁኑ ሰዓት እግሮቹ መንቀሳቀስ እንደማይችሉም ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መረጃ አመልክቷል።

ዘረኛው አገዛዝ በህዝብ ላይ የሚፈጽመው ግፍ በማናለብኝነት እስከቀጠለ ድረስ፥ ይህ አይነቱ ጥቃት እየጨመረ ብቻ እንደሚሄድ የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝ ግምታቸውን ገልጸዋል።

## በጋምቤላ ከዘረኛው አገዛዝ ጋር ትስስር ያለው ግለሰብ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሉ ተዘገበ

በኢትዮጵያ ዙሪያ የሚገኙ እና ከትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ጋር ልዩ ትስስር አላቸው ተብለው የሚታመኑ ግለሰቦች ከየማህበረሰቡ እየተገለሉ እና የጥቃት ሰለባዎች እየሆኑ እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አመልክቷል።

በቅርቡም በጋምቤላ ከዘረኛው አገዛዝ ጋር ትስስር ያለው ነጋዴ በድብደባ መገደሉን ዘገባው አሳይቷል።

እንደ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ ሶማሊ እና አፋር ባሉት ክልሎች፤ የአስተዳደር እና የንግድ እንቅስቃሴዎችን በበላይነት የተቆጣጠሩት የህወሃት ካድሬዎች መሆናቸውን የሚገልጸው ዘገባ፤ ይህ በየአካባቢው የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች በጥርጣሬ አይን እንዲታዩ አድርጓቸዋል ይላል። በተለይ በነዚህ ክልሎች የትግራይ ተወላጅ የሆኑና ከዘረኛው አገዛዝ ጋር ትስስር ያላቸው ግለሰቦች በመሬት ቅሚያ እንቅስቃሴ መሳተፋቸው እና እነሱ ለንግድ ስራቸው ለም መሬት እንዲወስዱ የአካባቢው ገበሬዎች ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉ መደረጉ ከፍተኛ ቅራኔን እየፈጠረ መሆኑ ታውቋል። በዚህም ምክንያት ሰዎች የትግራይ ተወላጆች ንብረት የሆኑ ንግድ ቤቶችን አገዛዙን ከመጥቀም ጋር እያስተሳሰሩ መጠጥ እና ቡና ቤቶቻቸውን መጎብኘት እያቆሙ ነው ተብሏል።

በጋምቤላ ክልል በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደለው ግለሰብም የትግራይ ተወላጅ እና በመሬት ቅምያ እንቅስቃሴ የተሳተፈ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ግለሰቡ በድንጋይ ተደብድቦ ከተገደለ በኋላ አይኖቹ ተጎልጉለው መውጣታቸውንም ዘገባው ገልጿል።

ዘጋቢያችን ያናገራቸው ዜጎች፥ ዘረኛው አገዛዝ የትግራይ ተወላጆችን ለእኩይ ተግባሩ መጠቀሙ በህዝቦች መካከል ያለውን ሰላም ከማደፍረስ አኳያ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዳለው ግልጽ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ አይነቱ ተግባር ወደፊት ከቁጥጥር ውጪ ሳይወጣ የትግራይ ልሂቃን ከተቀረው ህዝብ ሊወግኑ ይገባል ብለዋል። በየአካባቢው ተሰማርተው ዘረኛውን አገዛዝ በማገልገል ላይ ያሉትም እኩይ ተግባራቸውን እንዲያቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

ተኮላ ሃጎስ የተባሉና ከዚህ ቀደም የመለስ ዜናዊ አማካሪ የነበሩ የትግራይ ልሂቅ ከጥቂት ወራት በፊት ባወጡት ጽሁፍ፣ አገዛዙ ያለ ትግራውያን ድጋፍ በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጽመውን በደል ባላከናወነ ነበር ማለታቸውን እና እያገለገሉት ያሉ የትግራይ ተወላጆችም ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ጎን ቆመው እንዲታገሉ ጥሪ ማቅረባቸውን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

ይሁን እንጂ፥ የጋምቤላውን ክስተት በሚመለከት የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፤ ዘረኛው አገዛዝ የትግራይ ተወላጆችን እንደ መሳሪያ መጠቀሙ ጥርጣሬን እና ቅሬታን እያስፋፋ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ቢሆንም፣ ይህ አይነቱ ጉዳይ ሲዘገብ ግን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የዛሬ ስድስት አመት በአኟክ ኢትዮጵያውያን ላይ የጅምላ ግድያ ማድረግ ከመጀመሩ በፊት አንድ የትግራይ ተወላጅ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎ ሰውነቱ እንደተቆራረጠ ለህዝብ ማሳየቱን አስታውሰው፤ ያን ግለሰብ አኟኮች ለመግደላቸው ማስረጃ ባይኖርም፤ በወቅቱ በነሱ ላይ ጭፍጨፋ ሲፈጽም፣ ሌሎች ዝም ብለው እንዲመለከቱ ያስቻለው ግን በዛ ምክንያት ነበር ብለዋል።

**በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው . . .** (ከገጽ 1 የዞረ)

መገረፋቸውን የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክት ገልጿል። መግለጫው ጨምሮም፥ እናቲቱ ልብሳቸውን አውልቀው ጡቶቻቸው እስኪደሙ በኤሌክትሪክ ገመድ መገረፋቸው ከሁሉ የከፋው መሆኑን ገልጿል።

የኢትዮጵያው አገዛዝ በወ/ሮ እማዋይሽ ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ በአስቸኳይ እንዲያቆም እና አለማቀፍ የሰብአዊ ስምምነቶችን እንዲያከብርም ጥምረቱ ጥሪ አድርጓል። አንድ የጥምረቱ ተወካይ፥ ድርጅታቸው በተከሰተው ጉዳይ እጅጉን ቢቆጣም፣ አገዛዙ በአገሪቱ ውስጥ ከሚሰራው ስራ አኳያ አስገራሚ ግን እንዳልነበረ መናገራቸውን መግለጫው አክሎ አስታውቋል።

አለማቀፍ የኢትዮጵያውያን ሴቶች ድርጅትም ባወጣው መግለጫ በአገሪቱ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ሰቆቃ እጅጉን እንደሚያወግዝ ገልጾ፣ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሲቪል ድርጅቶችም ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ አቅርቧል።

ከድርጅቶች በተጨማሪ፥ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መድረኮች ቁጣና ሃዘናቸውን ሲገልጹ ቆይተዋል። በሆላንድ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ ለተለያዩ ድረ-ገጾች በላኩት መልክት፤ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በእናት ሃገር የሚፈጽመውን ሰቆቃ አስመልክቶ በቅርቡ የወጣውን ሪፖርት ካነበቡ በኋላ የተሰማቸውን ጥልቅ ሃዘን ቃላት እንደማይገልጹት እና እንቅልፍ መተኛት እንዳልቻሉ ገልጸዋል።

በዘረኛው አገዛዝ ቁጥጥር ስር በሚገኙ የደህንነት እና የህግ አስከባሪ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን "ከውርደት ህይወት ሞት ይሻለናል" በሚል ድፍረት፤ በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ በንጹሃን ላይ የሚፈጸመውን ሰቆቃ የሚያጋልጥ ሰፊ ሪፖርት አዘጋጅተው ማውጣታቸው ይታወቃል።

# ማስታወቂያ

የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ፥ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በስርጭቱ ላይ የሚፈጽምበትን አፈና ለመቋቋም የማያቋርጥ ጥረት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ምንም እንኳ በአሁኑ ሰአት ስርጭቶቹ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በጥራት የሚሰሙ ቢሆንም፤ ወደፊት ሊካሄዱ የሚችሉ ተጨማሪ የአፈና ጥረቶችን ለመቋቋም እና አድማጮች ጣቢያውን ለማግኘት ያላቸውን እድል ለማስፋት ሲል የስርጭት ሞገዶቹን ቁጥር ወደ ስምንት ከፍ አድርጎ፤ አንድ መካከለኛ ሞገድም የጨመረ ሲሆን፤ የስርጭት ሰአት ለውጥም ተደርጓል። አድማጮቻችን የሚከተሉትን ሞገዶች እና ሰአታት በመጻፍ ለምታውቋቸው ሁሉ እንድታስተላልፉ በአክብሮት እንጠይቃለን፡-

**ቅዳሜ፥ ታህሳስ 23፣ 2003** ዓ.ም. ጀምሮ የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ስርጭት በሳምንት ሶስት ቀናት፤ ማለትም ማክሰኞ እና ሐሙስ፤ እንደ ኢትዮጵያ ሰአት አቆጣጠር ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30፤ በድጋሚም ከሰዓት በኋላ ከ11 ተኩል እስከ 12 ሰዓት፤ ቅዳሜ እንደ ኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 2 ሰዓት ተኩል እስከ 3 ሰዓት፤ በድጋሚም ከሰዓት በኋላ ከ11 ሰዓት ተኩል እስከ 12 ሰዓት፤

በ358 ሜትር ባንድ በ837 ኪሎ ኸርዝ መካከለኛ ሞገድ ላይ

በ31 ሜትር ባንድ በ9700 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ41 ሜትር ባንድ በ7185፣ በ7175፣ በ7160፣ እና በ7120 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ49 ሜትር ባንድ በ5980 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ60 ሜትር ባንድ በ4760 ኪሎ ኸርዝ አጫጭር ሞገዶች ላይ

የሚተላለፍ መሆኑን እናስታውቃለን። ከዚህም በተጨማሪ፥ ስርጭታችንን በሳተላይት ለመከታተል ለምትፈልጉ፤ በአረብ ሳተላይት፣ በ11980 ፍሬኩዌንሲ ላይ በተመሳሳይ ሰአታት ልታገኙት እንደምትችሉ እናሳስባለን።

የግንቦት7 ድምጽ ሬዲዮ

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org